UNITED NATIONS
HUMAN RIGHTS COUNCIL

# በኢትዮጵያ እንደገና ባገረሸው ግጭት በ ቀጣይ ግፍ ሊፈጸም እንደሚችል የተባበሩት መንግስታት ባለሙያዎች አስጠነቀቁ

**መስከረም 09 2015**

**ጄኔቫ (መስከረም 08, 2015)** በሰሜን ኢትዮጵያ ዳግም ግጭት ሀገሪቱን ወደ ቀውስ እየከተተ በመሆኑ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ሲቪሎች ለተጨማሪ አሰቃቂ ወንጀሎች ስጋት ተጋልጠዋል ሲል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባለሙያዎች ቡድን ዛሬ አስታወቀ።
በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት በታህሳስ 2014 የተቋቋመው በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን በግጭቱ ውስጥ የተሳተፉ አካላት የጦር ወንጀሎችን እና የመብት ጥሰቶችን  ፈጽመዋል ብሎ የሚያሳምን ምክንያታዊ ምክንያቶች እንዳሉ በማጠቃለል **ሪፖርት** ባወጣበት ወቅት ነው። እ.ኤ.አ. ህዳር 2020 ጦርነት ከተቀሰቀሰበት ጊዜ ጀምሮ የሰብአዊ መብት አያያዝ፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት እና አጋሮቹ በትግራይ ክልል በሰብአዊነት ላይ ወንጀል መፈጸማቸውን ለማመን ምክንያታዊ የሆኑ ምክንያቶች እንዳሉ ኮሚሽኑ ደምድሟል።

ሪፖርቱ በትግራይ ያለውን አስከፊ ሁኔታ አጉልቶ የሚያሳይ ሲሆን የፌደራል መንግስት እና አጋሮቹ ከአንድ አመት በላይ የኢንተርኔት፣ የቴሌኮሚኒኬሽን እና የባንክ አገልግሎቶችን ጨምሮ ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዳያገኙ ሲከለከሉ ቆይቷል። የፌደራል መንግስትና አጋሮቹ ወደ ትግራይ የሚደረገውን ሰብዓዊ አገልግሎት ላይ ከፍተኛ ገደቦችን በመተግበራቸው 90% የሚሆነው ህዝብ ለከፍተኛ እርዳታ ጠባቂነት ተዳርጓል።

የኮሚሽኑ ሊቀ መንበር ካሪ ቤቲ ሙሩንጊ “በትግራይ ያለው ሰብአዊ ቀውስ በመጠን እና በቆይታ ረገድ አስደንጋጭ ነው” ብለዋል። "በመሠረታዊ አገልግሎቶች፣ የምግብ፣ የጤና አጠባበቅ እና የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት ላይ በስፋት መከልከል እና በሲቪል ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ነው፣ እናም ይህ በሰብአዊነት

ላይ የተፈፀመ ወንጀል ነው ብለን ለማመን በቂ ምክንያቶች አለን። የፌደራል መንግስት ረሃብን እንደ ጦርነት ዘዴ እየተጠቀመ ነው ብለን የምናምንበት በቂ ምክንያት አለን።

"የፌዴራል መንግሥት መሠረታዊ አገልግሎቶችን ባስቸኳይ ወደነበረበት መመለስ፣ የተሟላ እና ያልተገደበ ሰብዓዊ አገልግሎት መስጠት አለበት። የትግራይ ሃይሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ያለምንም እንቅፋት እንዲሰሩ ማድረግ አለባቸው" ሲሉ ወይዘሮ ሙሩንጊ አክለው ገልጸዋል።

ሪፖርቱ በጥር 2021 የኢትዮጵያ አየር ሃይል በደደቢት የተፈናቀሉ ዜጎችን ካምፕ በታጠቀ ሰው አልባ አውሮፕላን በመምታት በርካታ ህጻናትን ጨምሮ 60 በላይ የሚደርሱ ሰላማዊ ዜጎችን በገደለበት ወቅት የጦር ወንጀል ፈጽሟል ብሎ ለማመን ምክንያታዊ የሆኑ ምክንያቶችን አግኝቷል። ኮሚሽኑ ከሰኔ 2014 ጀምሮ የተካሄዱ ከ50 በላይ የአየር ጥቃቶችን ለይቷል፣ እነዚህም በሰላማዊ ሰዎች ወይም በሲቪል ንብረቶች ላይ ጉዳት ያደረሱ እና ተጨማሪ ምርመራ የሚሹ ናቸው።

የኮሚሽኑ አባል የሆኑት ስቲቨን ራትነር እንዳሉት፡ "የኢትዮጵያ ጦር ካለፈው ዓመት ወዲህ የአየር ድብደባ ለማድረስ ሰው አልባ አውሮፕላኖችን መጠቀሙ የግጭቱን ገጽታ ለውጦታል። በንድፈ ሀሳብ ፣ ድሮኖች ወታደራዊ ዓላማዎችን የበለጠ ትክክለኛ ኢላማ ማድረግ አለባቸው ። ነገር ግን የእነርሱ አጠቃቀም ሲቪሎችን ለአዳዲስ እና ለከፋ አደጋዎች እንዳጋለጣቸው ባደረግነው ጥናት አመልክቷል። ግኝታችን በተለይ ከነሃሴ ወር ጀምሮ በትግራይ የተፈፀመውን የአየር ድብደባ ህጻናትን ጨምሮ ሰላማዊ ዜጎችን ለሞትና ለአካል ጉዳት ካደረሰው ሪፖርቶች አንፃር ይመለከታል።

ኮሚሽኑ የትግራይ ሃይሎች በነሀሴ እና መስከረም 2021 እ. አ. አ.  ወር በቆቦ እና ጨና በተከሰቱት የአማራ ሰላማዊ ዜጎች ላይ መጠነ ሰፊ ግድያ፣አስገድዶ መድፈር እና ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ የጦር ወንጀል እና የሰብአዊ መብት ረገጣ ፈጽመዋል ብሎ ለማመን ምክንያታዊ የሆኑ ምክንያቶችን አግኝቷል።

ኮሚሽኑ በትግራይ በተፈጸሙ ሌሎች በርካታ መጠነ ሰፊ ግድያዎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ በማካሄድ ተጨማሪ ምርመራ እንደሚያስፈልግ ደምድሟል።

"መጠነ ሰፊ ግድያዎች በአማራና በትግራይ ብቻ የተገደቡ አይደሉም፣ በኦሮሚያና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ተመሳሳይ ክስተቶች እያሳሰቡን ነው። የከባድ ብጥብጥ መደበኛነት በጣም አሳሳቢ ነው" ሲሉ ሚስተር ራትነር አክለዋል።

ኮሚሽኑ በተጨማሪም ግጭቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ አስገድዶ መድፈር እና የፆታዊ ጥቃት ወንጀሎች “አስገራሚ” ደረጃ ላይ እንደሚገኙ፣ የትግራይ ሴቶች እና ልጃገረዶች በተለይ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ ሃይሎች እና በክልል ታጣቂዎች ጥቃት እና ጭካኔ ሲፈጸምባቸው ቆይቷል። አንዳንድ ጊዜ አጥቂዎቻቸው ሰብአዊነትን የሚያጎድፍ ንግግር ይጠቀሙ ነበር።

የኮሚሽኑ አባል ራዲካ ኩማራስዋሚ “በሰሜን ኢትዮጵያ ከፆታዊ ጥቃት የተረፉ ሰዎች አሰቃቂ ወንጀሎችን ተቋቁመዋል፣ እኛ ግን ከባህር በማንኪያ ብቻ ነው ያገኘነው ብለን እንሰጋለን” ብለዋል።
"በግጭቱ ወቅት የሚፈፀሙ ጥቃቶች እና በደሎች የሚያሳዩት አሰቃቂ ድርጊቶች በቦታው ላይ እንደማይገኙ እና ብሄርን መሰረት ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች እና ጥላቻ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። እንደዚህ አይነት ስሜቶች ቁጥጥር ሳይደረግባቸው እንዲያብቡ ብቻ ሳይሆን በመንግስት ባለስልጣናት እና በመገናኛ ብዙሃን በንቃት እንዲስፋፉ ይፋ ሆነዋል" ሲሉ ወይዘሮ ኩማራስዋሚ አክለዋል።

“በትግራይ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ለተፈጸመው መድፈር የበቀል እርምጃ እንደተወሰደባቸው ከአማራና ከኤርትራ የተረፉት የትግራይ ተወላጆች መግለጻቸው ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ጥቃትና ጥላቻ ምን ያህል መከፋፈልን እንደሚፈጥርና የጥቃት ዑደቶችን እንደሚቀጥል ያሳያል” ስትል ተናግራለች።

በግጭቱ የተሳተፉት ወገኖች በመጋቢት 2015 ጦርነቱ ለጊዜው እንዲቆም ተስማምተዋል። ነገር ግን በነሀሴ ወር መጨረሻ ጦርነት ተቀስቅሶ እንደገና ግጭት አስከትሏል እና ወደ ክልሉ የሚደረገው ሰብአዊ አገልግሎት እንዲቋረጥ አድርጓል። በርካታ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ጠቋሚዎች እና ለጭካኔ ወንጀሎች ቀስቅሴዎች መኖራቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ኮሚሽኑ የበለጠ የተጠናከረ ዓለም አቀፍ እርምጃዎችን እያሳሰበ ነው።

“በሰሜን ኢትዮጵያ ዳግም ጦርነት ባገረሸበት ወቅት ለተጨማሪ የሲቪል ስቃይ እና ተጨማሪ የጭካኔ ወንጀሎች አመላካች እውነተኛ አደጋ አለ” ብለዋል ወይዘሮ ሙሩንጊ። “ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዓይኑን ሳይጨፍን ይልቁንም ጦርነቱ እንዲቆም እና የትግራይ ሰብዓዊ ዕርዳታና አገልግሎት እንዲመለስ ጥረቶችን ማሳደግ አለበት። ይህን አለማድረግ ለኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ ጥፋት ከመሆኑም በላይ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ላይ ሰፊ አንድምታ ይኖረዋል።
ሪፖርቱ ሁሉም በግጭቱ ውስጥ ያሉ ወገኖች ጦርነቱን እንዲያቆሙ፣ ሰላማዊ ዜጎችን ለመጠበቅ ርምጃ እንዲወስዱ እና አጥፊዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ በመጠየቅ አስቸኳይ ምክረ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠናቋል።

ያበቃል

ለተጨማሪ መረጃ ጥያቄ እና ሚድያን፡ እባክዎትን ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ሰዎች ይጠይቁ፡ ሮናልዶ ጎሜዝ የICHREE rolando.gomez@un.org፡ +41 (0) 22 917 9711 ቶድ ፒትማን፡ የሚድያ አማካሪ፡ todd.pitman@un.org ማቲው ብራውን ፡ የHRC ህዝባዊ መረጃ ሃላፊ matthew.brown@un.org፡ ወይም ፓስካል ሲም፡ የICHREE ሕዝባዊ መረጃ ሚድያ ሃላፊ፡simp@un.org

የሰብኣዊ መብቶች ምክር ቤት በማህበራዊ ሚድያ ይከታተሉ፥ **ፌስቡክ** |**ትዊተር** | **ዩቱብ** | **ኢንስታግራም**